girl scouts nation's capital

# የ Girl Scout የቤተሰብ መመሪያ

**2024-2025**











# እንኳን ደህና መጡ!

የዚህን ዓመት የ Girl Scout የቤተሰብ መመሪያን ስለወሰዱ እናመሰግናለን። ይህ መመሪያ በ Girl Scout ውስጥ ስለሚኖርዎ ተሞክሮ ማወቅ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን፡ ከአስደናቂው ፕሮግራማችን ውጤቶች አንስቶ፣ እስከ ወጪ እና ደህንነትን የሚመለከቱ ጥቃቅን ዝርዝሮች ድረስ መመሪያ ይሰጥዎታል። የ Girl Scout ቡድኗን ሊደግፉ ስለሚችሉባቸው መንገዶች ሁሉ ይማራሉ፣ እንዲሁም የግልዎ የሆነ የ Girl Scout መመሪያ እንዲኖርዎት የቡድንዎን ዝርዝር ለማበጀት እና ለመጨመር ቦታ ይኖርዎታል።

# Girl Scouts የእርስዎ ቦታ ነው።

Girl Scouts በጥናት የተደገፈ ፕሮግራም ሲሆን ልጃገረዶች እና ወጣቶች እንዲዳብሩ እና ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ እድሎችን የሚሰጥ ፕሮግራም ነው። መረጃችን እንደሚያሳየው Girl Scouts በትምህርታቸው በላጭ ውጤት ያስመዘግባሉ፣ ስለወደፊት ኑሮዋቸው የበለጠ ብሩህ ተስፋ አላቸው እንዲሁም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ Girl Scouts ካልሆኑት ጋር ሲነጻጸሩ በህይወታቸው የበለጠ ስኬታማ ናቸው። ነገር ግን ብሩህ የወደፊት ተስፋን ከመገንባትም በላይ ነው። የእኛ ነው ብለው ስለሚያስቡት ቦታም ጭምር ነው—ቦታቸው ደግሞ Girl Scouts ነው።

### *ልጃገረዶች በ Girl Scouts ውስጥ ሲሳተፉ በ 5 ጠቃሚ መንገዶች ይጠቀማሉ፡-*

## ጠንካራ የማንነት ስሜት

ወጣቶች በራሳቸው እና በችሎታዎቻቸው ላይ እምነት ያላቸው ሲሆኑ አዎንታዊ ማንነቶችን ይመሰርታሉ።

## አወንታዊ እሴቶች

ወጣቶች በሥነ ምግባር፣ በቅንነት እና በኃላፊነት ይሰራሉ፣ እንዲሁም ለሌሎች አሳቢነትን ያሳያሉ።

## ጥረት የሚጠይቁ ነገሮችን ፍለጋ

ያለመሳካት እድል ያለው ነገር ቢሆን እንኳን፣ ወጣቶች በስልት ነገሮችን ደፍረው ይሞክራሉ፣ እንዲሁም ከስህተቶቻቸው ይማራሉ።

## ጤናማ ግንኙነቶች

ወጣቶች ስሜታቸውን በቀጥታ በመናገር እና ግጭቶችን ገንቢ በሆነ መንገድ በመፍታት ጤናማ ግንኙነቶችን ያዳብራሉ እንዲሁም ጠብቀው ያቆያሉ።

## የማህበረሰብ ችግር ፈቺነት

ወጣቶች ዓላማ እና ትርጉም ባለው መንገድ ለአለም አስተዋፅዖ የማድረግ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እንዴት መለየት እንደሚችሉ የማወቅ እና እነዚህንም ለመፍታት "ስልታዊ እቅዶችን" የመፍጠር ግብ አላቸው።




**ከ 110 አመታት** በላይ፣ Girl Scouts አለምን የተሻለች ቦታ የሚያደርጉ ደፋር፣ በራስ መተማመን ያላቸው እና ጠንካራ ምግባርን የተላበሱ ሴቶችን እየገነባ ነው።

# እሴቶቻችን፡ የ Girl Scout ቃል ኪዳን እና ህግ

## የ Girl Scout ቃል ኪዳን፡

*የሚከተሉትን ለማድረግ እንደምሞክር፣ ቃሌን እሰጣለሁ፡*
*ፈጣሪን እና ሀገሬን ለማገልገል፣*
*ሰዎችን ሁል ጊዜ ለመርዳት፣*
*እንዲሁም በ Girl Scout ህግ ለመተዳደር።*

**የ Girl Scout ን ቃል-ኪዳን ሲገቡ፣ እያንዳንዱ አባላት "ፈጣሪ" የሚለውን ቃል ከራሳቸው መንፈሳዊ እምነት ጋር በሚስማማ ቃል መተካት ይችላሉ።*

## Girl Scout ህግ፡


*የሚከተሉትን ለመሆን የተቻለኝን አደርጋለሁ*
*ሐቀኛ እና ፍትሃዊ፣*
*ተግባቢ እና ተባባሪ፣*
*በጎ እና አሳቢ፣*
*ደፋር እና ጠንካራ፣ እንዲሁም*
*ለምናገረው እና ለማደርገው ኃላፊነት የሚሰማኝ እንዲሁም*
*እራሴን እና ሌሎችን ለማክበር፣*
*የበላይ አስተዳደርን ለማክበር፣*
*ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠቀም፣*
*ዓለምን የተሻለ ቦታ ለማደረግ እንዲሁም*
*ለእያንዳንዱ Girl Scout እህት ለመሆን።*

---

# ከ Girl Scouts ጋር ማደግ

ጠንካራ፣ በራስ መተማመን ያላቸው እና ለስኬት ዝግጁ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ።

**እኛም እንደዚያው።**



# Girl Scout በተግባር ላይ፡- ቡድኖች እና ስብሰባዎች



**የ Girl Scout ቡድን** የ Girl Scout አስደናቂነት ህያው ሆኖ የሚጀምርበት ቦታ ነው። እንደ ቡድን፣ Girl Scouts ችግሮችን ለመፍታት፣ አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር፣ አዳዲስ ተልዕኮዎችን ለማቀድ እና ሌሎችንም ለማድረግ በጋራ ይሰራሉ።

ቡድኖች ማለት፡-

- የወጣቶች ቡድን (አብዛኛውን ጊዜ ከ10-12 የሚሆኑ Girl Scouts) እና እነሱን የሚደግፉ አዋቂዎች ናቸው።
- በተለምዶ በተወሰነ ማህበረሰብ የተደራጁ፣ ነገር ግን በዚያ ማህበረሰብ ያልተገደቡ - ክፍት ቦታ ያለው፣ ለትክክለኛው የክፍል ደረጃ የሆነ እና የቤተሰብዎን ፍላጎቶች የሚያሟላ ማንኛውንም ቡድን ይቀላቀላሉ!
- በክፍል ደረጃ የተደራጁ በ Girl Scouts ውስጥ አብረው እንዲያድጉ።

**ቡድኖች በወር ቢያንስ ሁለት ጊዜ ለአንድ ሰዓት ያህል** (በእድሜ ከፍ ላሉ ቡድኖች ጊዜው ይረዝማል) በቡድኑ አመራር በሚወሰን ጊዜ እና ቦታ ላይ ይገናኛሉ።

ቡድኖች የሚተዳደሩት **በቡድን ኮሚቴዎች ነው** ለቡድኑ እና ለሚኖረው ተሞክሮ ድጋፍ በሚያደርጉ በጎ ፈቃደኛ የወላጆች ቡድን። እያንዳንዱ ቤተሰብ ቡድኑን ለመደገፍ በተወሰነ አቅም በፈቃደኝነት መስራት ይጠበቅበታል!

# ለቡድኑ የ Girl Scout እና የቤተሰብ ሃላፊነት

ልክ እንደ ቡድን ስፖርት፣ የ Girl Scout ቡድኖችን ስኬት ከግብ ለማድረስ ወጣቶች፣ቤተሰቦች እና በጎ ፍቃደኞች አብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል። የ Girl Scout ቡድንን ሲቀላቀሉ በኃላፊነት የሚወስዷቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡

**Girl Scout ለቡድኑ የሚኖረው ኃላፊነት፡-**

- የ Girl Scout ን ቃል ኪዳን እና ህግ **መከተል**
- **አዳዲስ** ነገሮችን ለመሞከር ፍቃደኛ መሆን፣ **ለአዳዲስ** ተሞክሮዎች ዝግጁ መሆን እና **ለቡድኑ አጋሮች** ድጋፍ መሆን
- **በስብሰባዎች** እና ዝግጅቶች መገኘት እና መሳተፍ
- **ዝግጁ** መሆን እና በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ
- **የቡድን** መሪዎች እና ሌሎች በጎ ፈቃደኞችን ማክበር

**ወላጅ ወይም አሳዳጊ ለቡድኑ የሚኖረው ኃላፊነት፡-**

- **በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል፡** እያንዳንዱን ቡድን የሚያስተዳድሩ 9 የቡድን ኮሚቴ ሚናዎች አሉ። እያንዳንዱ ቤተሰብ በተወሰነ አቅም በፈቃደኝነት መስራት ይችላል እንዲሁም መስራት አለበት።
- **መመዝገብ፡** የእርስዎ Girl Scout (እና ማንኛቸውም የቤተሰብ በጎ ፈቃደኞች) የተመዘገቡ አባል መሆናቸውን ያረጋግጡ እንዲሁም አባልነትዎን በየዓመቱ በፀደይ ወቅት ያድሱ። ምዝገባው በመስመር ላይ (ኦንላይን) ሲሆን ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ የሚወስድ ነው።
- **በሰዓት መገኘት፡** ልጅዎ ከስብሰባዎች እና ዝግጅቶች በኋላ በሰዓቱ መወሰዷን ያረጋግጡ።
- **ግንኙነትን ማስቀጠል፡** ከቡድን መሪዎችዎ ጋር ይነጋገሩ፣ የፈቃድ ወረቀቶችን በሰዓቱ ያስገቡ እንዲሁም የቡድን መሪዎችም በጎ ፈቃደኞች መሆናቸውን ይረዱ።
- **የአከባቢ ድጋፍ፡** የአከባቢ ፕሮግራሞች እቅድ ላይ ለመርዳት የቡድኑ ወርሃዊ የአገልግሎት ስብሰባዎች ላይ፣ የኅዞ ሽርሽሮች እንዲሁም አስተዳደራዊ ተግባራት ላይ ይሳተፉ።
- **መሳተፍ፡** በቡድን ስብሰባዎች ላይ ምን እንደሚያደርጉ በመጠየቅ፣ እንዲዘጋጁ በመርዳት እንዲሁም የበጎ ፍቃደኛ መመሪያን በመመልከት የቡድን እቅዶች ላይ ወቅታዊ መረጃ እንዲኖርዎት በማድረግ የ Girl Scout ዎን ተሞክሮ ያበረታቱ።

# የ Girl Scout መሠረታዊ ተሞክሮ

## ወጣትነት፡

### የእውቅና አርማዎች እና ሽልማቶች፡-

- ቢያንስ 4 የእውቅና አርማዎች ወይም ሁለት የእውቅና አርማዎች እና የተልዕኮ ጉዞ እድል ማግኘት - አዲስ ነገር መሞከር!
- አዲስ ተሞክሮዎችን ለመሞከር ቡድኑ ቢያንስ 3 የመስክ ጉዞዎችን እንዲመርጥ ማድረግ
- ቢያንስ ሁለት የአገልግሎት ፕሮጀክቶችን ማስፈጸም
- በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በጀት ማዘጋጀት

### ሥራ ፈጣሪነት፡-

- በበልግ ወራት በ Fall Product በኩል ገቢ ማግኘት፡ ማድረግ ለሚፈልጉት ነገር ሰርተው እንዲያገኙ ግቦችን ማስቀመጥ
- ለፀደይ እና ለበጋ ወቅቶች ለቡድኑ የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ በ Cookie program ላይ ለመሳተፍ ግቦችን ማውጣት

### ከቤት ውጪ እንቅስቃሴዎች፡

- በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ከቤት ውጪ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ
- ምሳሌዎች፡-የውጪ እንቅስቃሴ ላይ ለተሳካ ተሳትፎ የሚሰጥ የእውቅና አርማ፣ የእግር ጉዞ፣ የመስክ ጉዞ፣ የአገልግሎት ፕሮጀክት፣ የጓሮ ሽርሽር፣ የቡድን ሽርሽር፣ በህብረት የሚደረግ የአዳር ቆይታ - የእድገት ደረጃን ማስታወስ!

### ወጎች፡-

- እንደ Thinking day (የማሰብ ቀን) ፣ Juliette Low's Birthday፣ Girl Scout Birthday፣ Investiture (ትውውቅ) ፣ Rededication (የቃል-ኪዳን እድሳት) ፣ Court of Awards (የእውቅና ክብረ-በዓል) እና ሌሎችንም የመሳሰሉ ዝግጅቶችን በማክበር የ Girl Scout ወጎችን ማክበር!

## የቡድን ኮሚቴ (የቤተሰብ በጎ ፈቃደኞች!):

### መሰረታዊ ነገሮች

- ለ 12 አባላት ቦታ ያለው ሆኖ ለመጀመር ቢያንስ 6 Girl Scouts ያለው ቡድን ማዋቀር
- ቡድኑ ከፍ ማለት ከፈለገ መሪዎችን ይጨምሩ!
- በወር ቢያንስ ሁለት ጊዜ ስብሰባ ማድረግ
- ቡድኑ በምቾት አብሮ የሚሰራበት አካባቢን መፍጠር

### በጎ ፈቃደኝነት

- ጠንካራ የቡድን ኮሚቴ እንዲቋቋም ለማስቻል እያንዳንዱ ቤተሰብ በተወሰነ ደረጃ በበጎ ፈቃደኝነት ከቡድኑ ጋር እንዲሰራ ማድረግ ቡድንን ለማንቀሳቀስ አጋርነት ያስፈልጋል!
- የቡድን በጎ ፈቃደኞች መኖራቸውን ለማረጋገጥ እና ለ Girl Scout ስኬቶች እውቅና ለመስጠት በአመት 2 የወላጅ ስብሰባዎችን ማካሄድ

### የገንዘብ አያያዝ

- የባንክ መግለጫዎችን ከደረሰኞች ጋር ለአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ በየወሩ ማቅረብ

**በአገልግሎት ክፍልዎ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን፡-**

- በእያንዳንዱ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ የቡድን ወኪል እንዲኖር ማድረግ
- የአካባቢ ፕሮግራሞችን ወይም አስተዳደራዊ ተግባራትን ለመደገፍ በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል
- ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ ማግኘት!

# ከቤት ውጪ ተልዕኮዎች

ከቤት ውጭ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የ Girl Scout ስር የሰደደ ማንነት ከሆነ ከ110 አመታት በላይ ሆኖታል። ለድንኳን ቆይታ፣ ለከፍተኛ ተልዕኮ፣ ለውሃ ስፖርት፣ ለቀናት ለሚቆዩ ጉዞዎች ወይም በሌሎች ምክንያቶች ወደ ውጪ የመውጣት ብዙ እድሎች አሉን። ለ Girl Scout ልጅዎ ከሚገኙ ከቤት ውጪ እንቅስቃሴ እድሎች መካከል አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡

**የካምፕ ንብረቶችን ቀን ላይ ሲጠቀሙ ይውላሉ ቀላል፣ ነፃ እና አቅራቢያዎ የሚሆን ነው**

ውጪው እርስዎ ከሚያስቡት በላይ ቅርብ ነው! Girl Scouts Nation's Capital ስምንት (8) የሚያማምሩ የካምፕ ንብረቶች አሉት - በእያንዳንዱ ካምፕ ውስጥ ካርታዎች እና የከፍተኛ ተልዕኮዎች ዝርዝር የሚገኝ ሲሆን እነዚህም በበጎ ፍቃደኛ የመገልገያ ስብስብ ውስጥ ይገኛሉ! እያንዳንዱ ንብረት Girl Scouts ብቻ የሚጠቀሙበት ነው። ቡድንዎን ለአንድ ቀን ይውሰዱ እና ጎጆዎችን፣ ከፍተኛ ተልዕኮዎችን እና የእግር ጉዞ መንገዶችን ይመልከቱ።

**ቡድኖች እና የአገልግሎት ክፍል የድንኳን ቆይታ ጉዞ (በህብረት የሚደረግ የአዳር ቆይታ)**

በየትምህርት አመቱ፣ ቡድኖች በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ላሉ Girl Scouts በአንዱ የካምፕ ንብረታችን ውስጥ የሚደረጉ የአዳር ቆይታዎችን ያቅዳሉ። በተጨማሪም የአገልግሎት ክፍሎች encampments (ብዙ ሰዎች በአንድ ቦታ ተሰብስበው የሚያሳልፏቸው የአዳር ቆይታዎች) ተብለው የሚጠሩ የአዳር ቆይታ ተሞክሮዎችን ይሰጣሉ። የቡድን እና የአገልግሎት ክፍል የህብረት የአዳር ቆይታዎች፣ ከቤት ውጪ ቆይታዎች/ከቤት ውጪ የምግብ ዝግጅት ላይ የሰለጠነ ባለሙያ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የተሳታፊዎችን ቁጥር ከፍ ለማድረግ ሲባል የአዋቂዎች ተሳትፎ ሊገደብ ይችላል።

**የበጋ ቆይታ ካምፕ እና የቀን/የምሽት ካምፕ**

የ Girl Scouts Nation's Capital ለአዳር ካምፕ የተሰሩ ስምንት የካምፕ ንብረቶችን ያስተዳድራል። የበጋ ወቅት የካምፕ ቆይታ ፕሮግራሞች የሚካሄዱት ከእነዛ ንብረቶች ውስጥ በአራቱ ሲሆን የቀን/የማታ ካምፖች በክልላችን ውስጥ ይከናወናሉ። የፕሮግራሞች ርዝመት እና ተሞክሮ የሚለያይ ሲሆን ምዝገባ በየዓመቱ ጃንዋሪ ወር ላይ ይጀምራል ከቤት ውጭ ከሚደረጉ ተልዕኮዎች፣ ስነ-ጥበብ እና STEM (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ሂሳብ) አንስቶ፣ እስከ የካምፕ ሙዚቃዎች፣ የጀልባ ጉዞ እና ሌሎችንም ጨምሮ በካምፕ ውስጥ ለእያንዳንዱ Girl Scout የሆነ ነገር ይኖራል። ካምፖቻችንን gscnc.org/camp ላይ ይመልከቱ።

# ተደራሽ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው እና ጠቃሚ

አባልነት

**25 ዶላር**

ለእያንዳንዱ አባል - እያንዳንዱ ቤተሰብ ለ አንድ Girl Scout አባል ቢያንስ 1 አዋቂ ማስመዝገብ አለበት።

የደንብ ልብሶች እና መጻሕፍት

**60 ዶላር**

My Girl Scout መገልገያ ስብስብ ይገኛል

የቡድን ክፍያ

**25 ዶላር**

ቡድኖች ህልማቸውን ከማሳካት በላይ ያገኛሉ!

አዲስ አባላት ከዚህ የተወሰነውን መጠን ወዲያው ሊከፍሉ ይችላሉ፣ ከዚያ በኋላ ግን፣ ቡድኖች የ Girl Scout ወጪያቸውን መሸፈኛ ገቢ የሚያገኙበትን መንገድ ያቅዳሉ።

# ማለም፣ ሰርቶ ማግኘት፣ ማድረግ

ሁሉም Girl Scouts የገንዘብ ቼክ ከማጻፍ ይልቅ ለ Girl Scout የሚውለውን ገንዘብ ሰርተው እንዲያገኙ ይበረታታሉ። ለምን? ለዚያ አስደናቂ የመስክ ጉዞ የዋለውን ገንዘብ ሰርታ እንዳገኘች የምታውቅ አንዲት የአፀደ ህፃናት ተማሪን ወይም ሰርታ ባገኘችው ገንዘብ ወደ ስዊዘርላንድ እየተጓዘች ያለች አንዲት የ 11ኛ ክፍል ተማሪን ያስቧት። የሥራ ፈጠራ ለ Girl Scouts ህይወትን የሚቀይሩ ተሞክሮዎችን የሚፈጥር ሲሆን ሌላ ፕሮግራም ሊያደርገው በማይችለው መልኩ የገንዘብ አያያዝ እውቀትን ይገነባል።

**አልሚው፣ ሰርተሽ አግኚው፣ አድርጊው። Girl Scout የሚለየው በዚህ ነው።**

የ Girl Scout Cookie ፕሮግራም እና Fall Product ፕሮግራም፣ Girl Scouts እንዲያልሙ፣ ሰርተው እንዲያገኙ፣ እንዲያደርጉ እንዲሁም አምስት ወሳኝ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ለመርዳት **የተዘጋጁ ዕድሎች ናቸው**:

**ግብ ማስቀመጥ**

የንግድ ሥራ እቅድ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል

**ውሳኔ መስጠት**

በጥልቀት ማሰብ እና ችግሮችን መፍታት

**የገንዘብ አያያዝ**

በቀጥታ የደንበኞችን ገንዘብ ማስተናገድ

**ማህበራዊ ችሎታዎች**

ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መገናኘት እና በራስ መተማመንን ማዳበር

**የንግድ ሥነ-ምግባር**

እንደ ሀቀኝነት እና ታማኝነት ያሉ አወንታዊ እሴቶችን ማዳበር

**FALL PRODUCT** ለዓመቱ መጀመሪያ እና አጋማሽ ገንዘብ ለማግኘት ከሴፕቴምበር እስከ ኖቬምበር ባለው ጊዜ ይካሄዳል።

የ **COOKIE ፕሮግራም** ለዓመቱ መጨረሻ እና ለሚቀጥለው ዓመት መግቢያ ገንዘብ ለማግኘት ከዲሴምበር እስከ ማርች ድረስ ይካሄዳል።

ሁለቱም ፕሮግራሞች በአካል እና በምናብ (ቨርቹዋል) ለሚደረግ ተሳትፎ እድሎች አሏቸው!

የገቢው 100% ቡድኖችን እና Girl Scouts ን ለመደገፍ በአካባቢው ይቆያል!

የቡድን ገቢ ለቡድኑ በጋራ ጥቅም ላይ ይውላል - በተሸጠው መጠን ላይ በመመስረት ማንም ተጨማሪ ገንዘብ የማግኘት መብት የለውም።

# የገንዘብ ድጋፍ

አካታችነት ከ1912 ጀምሮ የ Girl Scouts ዋና መርህ ነው። ሁሉም ሰው Girl Scout መሆን ይችል ዘንድ ምክር ቤታችን እርዳታን ለሚሹት የሚከተሉትን አይነት የገንዘብ ድጋፎች ሲያቀርብ ኩራት ይሰማዋል።

## ዓመታዊ የ GSUSA አባልነት ክፍያዎች

ለወጣቶች እና ለአዋቂ በጎ ፈቃደኞች፣ የ GSUSA ዓመታዊ የአባልነት ክፍያዎች እገዛ ይገኛል።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** www.gscnc.org ላይ በመለያዎ ይግቡ፣ Girl Scout ልጅዎን ወይም አዋቂ በጎ ፈቃደኛን ያስመዝግቡ እና ስርዓቱ ክፍያ ሲጠይቅዎ 'የገንዘብ ድጋፍ' የሚለውን ይምረጡ።

የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎች በእያንዳንዱ የስራ ቀን ይገመገማሉ። ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ ወላጆች ኢሜይል ይደርሳቸዋል።

*Girl Scouts ልጆቻቸውን ወክለው ለአባልነት የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ የሚችሉት አሳዳጊዎች ብቻ ናቸው። በወላጆች ወይም በሌሎች አዋቂዎች ስም የቡድን መሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ አይችሉም።*

## የደንብ ልብሶች፣ መጽሃፎች እና የቡድን ክፍያዎች

የደንብ ልብሶች፣ መጽሃፎች እና የቡድን ክፍያ እገዛ ለተመዘገቡ Girl Scout ወጣቶች እና የቡድን መሪዎች ይገኛሉ።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** ከኦገስት 15 እስከ ኤፕሪል 15 ባሉት ቀናት gscnc.org ላይ በመግባት፣ 'አባላት' የሚለውን በመጫን በመቀጠል 'ፎርሞች እና ሰነዶች'ን ተጭነው 'የገንዘብ እገዛ ለደንብ ልብሶች፣ መጽሃፎች እና የቡድን ክፍያ 'የሚለውን በመምረጥ የመስመር ላይ (ኦንላይን) ጥያቄዎን ያስገቡ።

የቡድን ክፍያ ቼኮች ወደ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ መላክ አለባቸው።

የደንብ ልብሶች እና መጽሃፎችን ለጠያቂው ግለሰብ በቀጥታ መላክ ይቻላል።

## የኋላ ታሪክ ማጣሪያ ክፍያ

ለኋላ ታሪክ ማጣሪያ ክፍያ እገዛ ተዘጋጅቷል።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** የኋላ ታሪክ ምርመራን ለሚጠይቅ ሚና እንደ አንድ አዋቂ በጎ ፈቃደኛ ከተመዘገቡ በኋላ፣ ከ Sterling Volunteers፣ በ 'The Advocates' ስም የቀረበ መጥሪያ/ማሳወቂያ ይፈልጉ። ሁለት የገጽ አገናኞች አሉ፤አንዱ ቅጹን ለመሙላት እና ክፍያውን ለመክፈል፤ አንዱ ደግሞ ለክፍያው እገዛን እንዲጠይቁ የሚያስችልዎ ነው።

## የነጻ ስልጠና ማመልከቻ

ለፕሮግራሞች ውጤታማነት ከሚሰጥ የአዋቂዎች ትምህርት ጋር ለሚያያዙ ክፍያዎች በጎ ፈቃደኞች፣ የገንዘብ ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ይህ ለእያንዳንዱ ኮርስ በዓመት፤ በአንድ ቡድን፤ ለአንድ በጎ ፈቃደኛ ይገኛል።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** gscnc.org ላይ በመሄድ 'አባላት' በመቀጠል 'ቅጾች እና ሰነዶች'ን በመጫን እና 'የነጻ ስልጠና ማመልከቻ' የሚለውን በመምረጥ የመስመር ላይ ጥያቄ ያቅርቡ

## የፕሮግራም ድጎማዎች

በአንድ የተወሰነ እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ ለተመዘገቡ Girl Scouts (ወጣቶች ወይም አዋቂዎች) የተዘጋጁ የፕሮግራም ድጎማዎች አሉ።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** ቅጹን ሞልተው ያስገቡ (ወደ gscnc.org በመሄድ 'አባላት' የሚለውን በመቀጠል 'ቅጾች እና ሰነዶች' የሚለውን በመጫን እና 'ለአጠቃላይ ፕሮግራም የድጎማ ማመልከቻ' የሚለውን በመምረጥ ይገኛል)

ይህ ቅጽ ዝርዝር በጀቶችን እና/ወይም የጊዜ ሰሌዳዎችን የሚጠይቅ ሲሆን በአጠቃላይ ከ 6-8 ሳምንታት በፊት መቅረብ አለበት።

## የቡድን፣ የጋራ ወይም የግለሰብ ፕሮግራም የብድር አገልግሎት

የፕሮግራም ብድሮች የሚሰጡት ክፍያ መፈጸም ባለበት ወቅት ለብቁ የ Girl Scout ወጪ ገንዘብ በማይገኝበት ጊዜ ነው።

**ጥያቄ ለማቅረብ:** ቅጹን ሞልተው ያስገቡ (ወደ gscnc.org በመሄድ 'አባላት' የሚለውን በመቀጠል 'ቅጾች እና ሰነዶች' የሚለውን ይጫኑ)

የGirl Scout Nation's Capital ቤተሰብ የመስጠት ዘመቻ፣ **SHARE፣** ለአባሎቻችን የገንዘብ እገዛ ድጋፍ ይሰጣል። ይህንን ዘመቻ **gscnc.org/donate** ላይ መደገፍን ከግምት ውስጥ ያስገቡ

# ቤተሰብዎ እና Girls Scout

Girl Scouts በበጎ ፈቃደኞች የሚመራ፣ በበጎ ፈቃደኞች የሚንቀሳቀስ ነው፡ ከበጎ ፈቃደኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ እስከ ሹፌር/አጃቢዎች ድረስ።

ሁሉም ቤተሰቦች ተሞክሯቸውን ጥሩ ለማድረግ ለማገዝ በሆነ መልክ በበጎ ፈቃደኝነት ያገለግላሉ!

ከፍተኛ የወላጅ ተሳትፎ ያላቸው ቡድኖች አብረው የመቆየት እድላቸው ሰፊ ነው፡ማለትም Girl Scout ልጅዎ ከፍተኛ የሚባለውን የአመራር ጥቅም ታገኛለች ማለት ነው!

ከእርሷ ቡድን ጋር በበጎ ፈቃደኝነት መስራት ማለት ከ Girl Scout ልጅዎ ጋር ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ፣ ጓደኞቿን እና ማህበረሰቧን ለመተዋወቅ እንዲሁም ከእነሱ ጋር ለቀጣይ ብዙ አመታት የአዳዲስ ተልዕኮ ተሞክሮዎችን ለማግኘት እንደ እድል ሊጠቀሙበት የሚችሉት ነው!

"[የተንከባካቢ] ተሳትፎ ለቡድኑ ማንነት መሰረት ነው።"

የ Girl Scout ካዴት ተንከባካቢ

"Girl Scouts አስደሳች የሆነው እናቴ የቡድኑ መሪ በመሆኗ ነው።"

የ Girl Scout ዴይዚ




# የቡድን ኮሚቴዎች

እያንዳንዱ ቤተሰብ በቡድኑ ኮሚቴ ውስጥ አንድ ሚና በበጎ ***ፈቃደኝነት ይወስዳል።*** አንድ ሰው ወይም ቤተሰብ ከአቅሙ በላይ እንዳይጨናነቅ ወይም ኃላፊነት እንዳይሸከም የቡድን ኮሚቴው በአንድነት የቡድኑን ተሞክሮ የተለያዩ ክፍሎች አቅዶ ተግባራዊ ያደርጋል። የቡድን ኮሚቴው ቁልፍ አስተባባሪዎች የቡድን መሪዎች ሲሆኑ ተጨማሪ ኃላፊነቶችን እንደ አስፈላጊነቱ ለቡድን ኮሚቴው ያስተላልፋሉ።

ስልጠና እና ድጋፍ ለእያንዳንዱ የስራ ድርሻ ዝግጁ የሆነ እና የሚያስፈልግ ሲሆን ቡድኑ ለማለም፣ ሰርቶ ለማግኘት እና ለማድረግ የሚያስችለውን የአመራር ተሞክሮ ማግኘቱን ቤተሰቦች በአንድነት ያረጋግጣሉ!

ሁሉም ቡድኖች በመነሻነት፣ ሁለት የቡድን መሪዎችን እና የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪን ጨምሮ የስጋ ዝምድና፣ የጋብቻ ወይም የቤተሰብ ግንኙነት በሌላቸው ቢያንስ አራት አዋቂዎች ይመሰረታሉ። **እያንዳንዱ ቤተሰብ በፈቃደኝነት ከ Girl Scout ቡድኑ ጋር በተወሰነ አቅም መስራት ይጠበቅበታል።**

ቡድኑን እየረዱ ያሉ ነገር ግን የተሰየመ የኮሚቴ ሚና የሌላቸው አዋቂዎች እንደ የጓደኞች እና የቤተሰብ በጎ ***ፈቃደኛ መመዝገብ ይችላሉ።*** ይህም የኋላ ታሪክ ማጣሪያ የማያስፈልገው ብቸኛው ሚና ነው።

***ሁሉም ሌሎች ሚናዎች በቡድኑ ውስጥ ላሉት ወጣቶች እና አዋቂዎች ደህንነት ሲባል የኋላ ታሪክ ማጣሪያ ያስፈልጋቸዋል።***

| | |
|---|---|
| ቤተሰባችን ይህንን የቡድን ኮሚቴ ሚና መርጧል፡- | |

# የቡድን ኮሚቴ ሚናዎች

## የቡድን መሪዎች

Girl Scouts ውሳኔዎችን እና ምንምን የእውቅና አርማዎችን፣ እንቅስቃሴዎች እና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ማድረግ እንደሚፈልጉ እንዲወስኑ ይረዳሉ።

የስብሰባ ዕቅዶች፣ የቁሳቁስ ዝርዝሮች እና ሌሎችም የሚያካትተውን የበጎ ፈቃደኞች የመገልገያ ስብስብን በመጠቀም የስብሰባ ፕሮግራሞችን ይመራሉ!

ለቡድኑ የአስተዳደር አስተባባሪ ሆነው ያገለግላሉ እንዲሁም የተቀሩትን ኃላፊነቶች ለቡድኑ ኮሚቴ ውክልና ይሰጣሉ።

ስልጠና ይወስዳሉ፡የመጀመሪያ ደረጃ (1 ክፍል በቀጥታ፣ 1 ክፍል በግል መርሃ-ግብር)፣ የቡድን የገንዘብ አስተዳደር እና የ DEIA (ብዝሃነት፣ እኩልነት፣ አካታችነት፣ ተደራሽነት) ቁርጠኝነት ስልጠና።

*ሁሉም ቡድኖች ቢያንስ ሁለት ዝምድና የሌላቸው አዋቂ የቡድን መሪዎች ሊኖሯቸው ይገባል፣ ከነዚህም አንዷ በሁሉም የ Girl Scout ቡድን ስብሰባዎች ላይ የምትገኝ ሴት መሆን አለባት። ማንኛውም አዋቂ በየትኛውም ጊዜ ከአንድ ወጣት ጋር ብቻውን አይሆንም።*

## የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ

በ Girl Scout መመሪያ መሰረት የበጀት ዝግጅት እና ገቢ ማግኛ እቅድ ማውጣት ላይ ቡድኑን ያግዛል።

ለሁሉም የቡድኑ ቤተሰብ ገቢ እና ወጪን በየጊዜው ያሳውቃል።

በቡድኑ የባንክ ሂሳብ ላይ ይፈርማል እንዲሁም ወርሃዊ ሰነዶችን ለአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ ያቀርባል።

ዓመታዊ የኦንላይን ስልጠና ይወስዳል።

## የቡድን የ Cookie አስተዳዳሪ እና የቡድን የ Fall Product አስተዳዳሪ

ቡድኑ ማድረግ ለሚፈልጋቸው ተግባራት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ግቦችን እንዲያስቀምጥ እንዲሁም በ Fall Product እና Cookie ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፍ ያግዛል።

ትዕዛዞች ማስገባት እና ማከፋፈል እንዲሁም የዳስ ጣቢያዎች መምረጥን ጨምሮ የፕሮግራሙን አስተዳደራዊ ክፍሎች ያስተዳድራል።

ዓመታዊ የኦንላይን ስልጠና ይወስዳል።

## ከቤት ውጪ ቆይታዎች/ከቤት ውጪ የምግብ ዝግጅት አዋቂ ባለሙያ

ተራማጅ ከቤት ውጪ ተሞክሮዎች እቅድ ላይ ቡድኑን ያግዛል።

ምግብ ማብሰል እና ውጪ መተኛትን ጨምሮ ከቤት ውጪ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወቅት ደህንነትን ያረጋግጣል።

የአንድ ጊዜ ስልጠና ይወስዳል፡ ለምግብ ዝግጅት በአካል የሚሰጥ ስልጠና፣ ወይም ለአዳር ቆይታ እና ምግብ ዝግጅት የአንድ ሌሊት ጥምር ስልጠና ይወስዳል።

## የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ሰጪ

የመጀመሪያ እርዳታ መስጠት ሊያስፈልግ በሚችልባቸው የካምፕ ጉዞዎች እና ሌሎች ጉዞዎች ላይ ቡድኑን ያጅባል።

ምክር ቤቱ እውቅና በሰጠው ስልጠና አቅራቢ ስልጠና ይወስዳል ወይም ነባር የህክምና ትምህርት ማረጋገጫ ያለው (ሀኪም፣ ነርስ፣ የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ ፣ ወዘተ)።

## ሹፌር /አጃቢ

Girl Scouts የመስክ ጉዞዎችን እንዲያቅድ እና እንዲመራ ይረዳል።

የጤና ቅጾች እና የፈቃድ ወረቀቶችን የመሳሰሉ የደህንነት ሰነዶች መሞላታቸውን ያረጋግጣል።

## የቡድን SHARE ሊቀመንበር

ለ SHARE (በክልላችን ውስጥ Girl Scoutingን የሚደግፍ የቤተሰብ የመስጠት ዘመቻ) ድጋፍ የማድረግ እድል ሁሉም ቤተሰቦች እያገኙ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

# የ Girl Scout በጎ ፈቃደኞች እና የወላጅ መገልገያዎች

በ Girl Scouts ውስጥ የሚያገኟቸው ብዙ ነገሮች አሉ፣ ነገር ግን አያሳስብዎት ለወላጆች እና በጎ ፈቃደኞች የተዘጋጁ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት፣ የበጎ ፈቃደኝነት ጊዜዎን ለማሳለጥ እና የቡድንዎን ተሞክሮ ለማበልጸግ የሚውሉ ብዙ መገልገያዎች አሉን። ለቡድን ኮሚቴ አባላት የተዘጋጁ አንዳንድ መገልገያዎች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡

## ሕትመቶች፡-

**Girl Scout Insider** (Girl Scout ውስጥ አዋቂ)፡ ሊመዘገቡባቸው የሚችሏቸው የ Girl Scout ፕሮግራሞች ዝርዝር በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ቤት ይላካል!


**Volunteer Essentials** (የበጎ ፈቃደኞች መመሪያ መጽሐፍ)፡ የበጎ ፈቃደኝነት፣ የካምፖች፣ የቡድን ገንዘብ አያያዝ እና ሌሎችም መመሪያ በኦንላይን ላይ የሚገኝ እንዲሁም ለቡድን መሪዎች በየአመቱ በወረቀት ቅጂዎች ይሰጣል

**Safety Activity Checkpoints** (የደህንነት እንቅስቃሴ ፍተሻዎች)፡ ለሁሉም ተግባራት የደህንነት መስፈርቶች በኤሌክትሮኒካዊ ቅርጸት gscnc.org ላይ ይገኛል

## የመስመር ላይ (ኦንላይ) መገልገያዎች

**የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብ (VTK)**፡ የስብሰባ መመሪያዎች ከንድፎች እና የግዢ ዝርዝሮች ጋር፣ የተሳትፎ መከታተያዎች፣ የእውቅና አርማ እና ስኬት መከታተያዎች - በቡድን መሪዎች ሊስተካከል እና በሁሉም ወላጆች ሊታይ የሚችል!

**gsLearn**: ለምናባዊ ስልጠና የመስመር ላይ መማሪያ ስርዓት እንዲሁም በአካል ለሚሰጥ ስልጠና መመዝገቢያ። አስፈላጊ ስልጠና እንዲሁም ማንኛውንም የሚፈልጉትን የማበልጸግያ ስልጠና ይውሰዱ!




## የፕሮግራም ዝግጅቶች፡-

በፕሮግራም ዝግጅቶች በኩል የቡድን ተሞክሮዎን ያበለጽጉ! ከምንታወቅባቸው ዝግጅቶች (እንደ የ Girl Scout ቀን Air & Space Museum ወይም የካምፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ) አንስቶ እስከ በፕሮግራም አጋሮች የሚተዳደሩ አስደናቂ ፕሮግራሞች ድረስ፣ ለሁሉም የሚሆን ነገር አለ!

መጪ ፕሮግራሞችን በ Girl Scout Insider ውስጥ ይመልከቱ፣ ወይም gscnc.org ን በመጎብኘት እና 'አባላት' በመቀጠል 'ክስተቶች'ን በመጫን በአቅራቢያዎ ያሉ ዝግጅቶች ያግኙ። የሚወዱትን ነገር ማግኘትዎ የማይቀር ነው!

# የትኛዋም Girl Scout ብቻዋን አትሄድም፡ የአካባቢዎ ድጋፍ ሰጪ

በ Girl Scout ውስጥ ቦታ የሚኖራት ብቸኛ ሰው የእርስዎ ልጅ ብቻ አትሆነም - ቡድንዎም የራሴ የሚለው ቤት ያገኛል። ያም ቤት የአገልግሎት ክፍል ይባላል፡ ለ Girl Scout ቡድንዎ አስደናቂ ተሞክሮ ለመስጠት አብሮ የሚሰራ የአከባቢው የቡድኖች ስብስብ። የአገልግሎት ክፍሎች፡-

- አዳዲስ ቤተሰቦች እና ቡድኖች ወደ Girl Scouts ሲቀላቀሉ ያግዛል
- ቡድኖች በመመሪያዎች መሰረት መስራታቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል
- የቡድኑን ተሞክሮ ለማበልጸግ የአካባቢ ፕሮግራሞችን ያቅዳል፡የአዳር ቆይታ፣ ወጎች፣ የእውቅና አርማ ቀናት፣ ወይም ተጨማሪ!
- ትስስር ለመዘርጋት እና ለበጎ ፈቃደኞች ድጋፍ ወርሃዊ ስብሰባ ያዘጋጃል

የአገልግሎት ክፍልዎ ልክ እንደ እርስዎ የአገልግሎት ክፍሉን ለማስቀጠል በሚያግዙ የአካባቢ በጎ ፈቃደኞች ቡድን ይመራል። ከእነዚህ ቁልፍ በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞች መካከል አንዳንድ ምሳሌዎች፡-

- **የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎች፡** ለአገልግሎት ክፍል ወርሃዊ ስብሰባዎችን ያካሂዳሉ፣ አዳዲስ መረጃዎችን ለመጋራት፣ ግጭት ለመፍታት እና ጠንካራ የአገልግሎት ክፍል ቡድን ለመመልመል በምክር ቤት ደረጃ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋሉ
- **የአገልግሎት ክፍል መዝጋቢ፡** በምዝገባ እና በኋላ ታሪክ ማጣሪያ ሂደት ላይ ቤተሰቦችን ይመራል እንዲሁም በጸደይ አመታዊ የእድሳት ሂደት ወቅት ድጋፍ ያደርጋል
- **የአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ፡** አዳዲስ ቡድኖች የባንክ ሒሳቦችን እንዲከፍቱ ያግዛል፣ ወርሃዊ የባንክ መግለጫዎችን እና ደረሰኞችን ከቡድኖች ይሰበስባል፣ እንዲሁም የገንዘብ አሰራር ሂደቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል
- **የአገልግሎት ክፍል እንግዶች ተቀባይ ባለሙያ፡** ሁሉንም አዲስ የቡድን በጎ ፈቃደኞች ይቀበላል እንዲሁም ከስልጠና እና ድጋፍ ጋር ያገናኛቸዋል
- **የአገልግሎት ክፍል ቡድን አስተባባሪዎች፡** ከትምህርት ቤት ወይም ከአምልኮ ቤት ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ቡድኖችን በማቋቋም እና በማሻሻል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አዲስ አባላትን በቡድን ውስጥ በመመደብ ያግዛል

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ሲኖሩዎት በመጀመሪያ የሚሄዱት ወደ የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎ ነው። አድራሻቸውን **በገጽ 12** ላይ ማስቀመጥ ይችላሉ።

# በ Girl Scouting ውስጥ ደህንነት አጠባበቅ

Girl Scouts Nation's Capital ከደህንነት የበለጠ አስፈላጊ የሚለው ነገር የለም። ከመጀመሪያው ሊያውቋቸው የሚገቡ ጥቂት የደህንነት መመሪያዎች በቀጣይ ተጠቅሰዋል፡

- **የደህንነት ጥምርታዎች፡**- Girl Scouts በሚሰበሰቡበት ወቅት የልጆቻችንን ደህንነት ለማረጋገጥ፣ በትንሹ ሁል ጊዜ 2 አዋቂዎች አብረዋቸው የሚኖሩ ሲሆን አንዷ ሴት ነች። አንድም አዋቂ ከልጅ ጋር ብቻውን እንዲሆን ፈጽሞ አይፈቀድለትም። በቂ ቁጥጥርን ለማረጋገጥ ለሰፋፊ ቡድኖች ወይም ስብሰባዎች ተጨማሪ በጎ ፈቃደኞች ያስፈልጋሉ።
- **የኋላ ታሪክ ማጣሪያ፡** ከልጆች ጋር በመደበኛነት የሚሰሩ፣ በአዳር ዝግጅት ላይ የሚሳተፉ ወይም በ Girl Scouts ውስጥ ገንዘብ የሚይዙ በጎ ፈቃደኛ አዋቂዎች በታመነው አገልግሎት አቅራቢያችን Sterling Volunteers በኩል በኦንላይን የኋላ ታሪክ ማጣሪያን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል።
- **የኃላፊነት መድን፡**- የቡድን ስብሰባም ይሁን የካምፕ ወይም የመስክ ጉዞን መሰል የ Girl Scout ዝግጅቶች ላይ በመደበኛነት የሚሳተፉ ሁሉም አባላት፣ በእኛ የኃላፊነት መድን ስር ሽፋን የሚያገኙ አባላት ሆነው መመዝገብ አለባቸው።
- **ስልጠና፡**- ሁሉም በጎ ፈቃደኞች፣ ከአዋቂ ትምህርት መምህሮቻችን፣ በአገልግሎት ክፍል ደረጃ ከሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞች፣ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ወቅት እውቅና ካላቸው አቅራቢዎች ስልጠና እና መመሪያዎችን ይወስዳሉ።

*ሙሉ የደህንነት መመሪያዎችን ከበጎ ፈቃደኞች መመሪያ መጽሐፍ እና በድረ-ገፃችን* gscnc.org *ላይ ማግኘት ይችላሉ።*

# Girl Scout ውስጥ የሚካሄዱ ነገሮችን መከታተል

## የቡድን ግንኙነት

ውጤታማ የቡድን ግንኙነት መኖሩ ሁሉም ቤተሰቦች ስለመጪ ስብሰባዎች እና ዝግጅቶች የሚያውቁ መሆኑን እና የቡድን መሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እያገኙ መሆኑን ያረጋግጣል።

እያንዳንዱ ቡድን የሚስማማውን የመገናኛ ዘዴ ይመርጣል። በ Girl Scouts Nation’s Capital ለቡድንዎ የቡድን 'ስብሰባ' እንዲያዘጋጁ እንመክራለን (ከዚህ በታች ያለውን Rallyhood ይመልከቱ)። በተጨማሪም የቡድን መሪዎች የስብሰባ ማሳሰቢያዎችን እና ዕቅዶችን በበጎ ፈቃደኞች የመገልገያ ስብስብ በኩል መላክ ይችላሉ (ለበለጠ መረጃ ገጽ 8 ን ይመልከቱ)።

ያስታውሱ፣ ከቤተሰብ ኃላፊነት ውስጥ አንዱ ከቡድን መሪዎች ጋር መገናኘት ነው!ቡድንዎ እንዴት እንደሚገናኝ ማወቅዎን እና ያንን መድረክ በመደበኛነት መመልከትዎን ያረጋግጡ።

## የአገልግሎት ክፍል ዝግጅቶች እና ክስተቶች

የአካባቢዎ የአገልግሎት ክፍል አዳዲስ መረጃዎችን፣ መጪ በአካባቢ እና በምክር ቤት-ደረጃ የተዘጋጁ ዝግጅቶችን ለማጋራት እና በቡድኖች መካከል ትስስር ለመፍጠር ወርሃዊ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል። የአገልግሎት ክፍል ስብሰባዎች በ Girl Scouts ውስጥ ስለሚከናወኑት ነገሮች አጠቃላይ እይታ ለማግኘት እና ልክ እንደ እርስዎ የበጎ ፈቃደኞችን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ካሉት ምርጥ መንገዶች አንዱ ነው።

እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል የራሱ የመገናኛ ዘዴ ያለው ሲሆን የራሱን የስብሰባ ቀን እና ሰዓት ያዘጋጃል። ከእርስዎ የአገልግሎት ክፍል የመገናኛ መሳሪያ ጋር ለመገናኘት እና ቀጣይ ስብሰባ ሲኖር ለማወቅ የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎን ያግኙ (ስለ አገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 9 ይመልከቱ)።

የአገልግሎት ክፍሎች የአካባቢ ዝግጅቶችን ለማቀድ አብረው ይሰራሉ። እንደ ዓለም አቀፍ የማሰብ ቀን ወይም VIP እና Me Dance ያለ ልዩ ዝግጅት ላይ ፍላጎት አልዎት? የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎን ያነጋግሩ እና በኮሚቴ ውስጥ ዝግጅቱን በማቀድ ለማገልገል ሀሳብ ያቅርቡ!

# Rallyhood

Rallyhood የ Girl Scouts Nation’s Capital የመስመር ላይ የማህበራዊ ሚዲያ መገልገያ ነው። Rallyhood ቡድኖች መረጃ የሚለዋወጡበት፣ ፎቶዎችን የሚለጥፉበት፣ ምዝገባዎችን የሚያካሂዱበት እና የጋራ የቀን መቁጠሪያ የሚይዙበት የግል ቡድኖች መድረክ ያቀርባል።

የ Girl Scouts Nation’s Capital ለተወሰኑ ቡድኖች መረጃን ለማጋራት በርዕስ ላይ የተመሰረቱ ስብሰባዎችን ያቀርባል፣ ለምሳሌ፡-

- ዴይዚ፣ ብራውኒ፣ ጁንየር ሬሊይ: ለ K-5 Girl Scouts መረጃ እና ዝግጅቶች
- የታዳጊዎች ፕሮግራም ስብሰባ፡ ለ6ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለመረጃ እና ዝግጅቶች
- ከቤት ውጪ ተግባራት እና ከፍተኛ ተልዕኮዎች ስብሰባ፡ Girl Scout ን ከቤት ውጪ ለማግኘት
- የማህበረሰብ አገልግሎት፡ ለአገልግሎት ፕሮጀክቶች ሀሳቦችን እና እድሎችን ለማጋራት
-



# Girl Scout መሆንሽን ማሳየት፡- የደንብ ልብሶች፣ መጽሃፎች እና ሌሎችም

## ለ Girl Scout የደንብ ልብስ ምን ያስፈልጋል?



የደንብ ልብስ ለመልበስ፣ አንድ Girl Scout የሚያስፈልጋት ነገር ይፋዊ **የ Girl Scout መለያ አርማ ብቻ ነው**። መለያ አርማዎች የቡድን ስብሰባዎች ከተጀመሩ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በትውውቅ ሥነ ሥርዓት ላይ ይሰጣሉ።

የተገኙ እውቅናዎች (**አርማዎች**) የGirl Scout ልጅዎን እድገት እና ምን እየተማረች እንዳለች ያሳያሉ። **ሰደርያዎች** እና **መቀነቶች** የደረሱበትን ደረጃ ለመመዝገብ እና ለማሳየት በጣም ጥሩ ናቸው።

**እነዚህን አስፈላጊ** ዕውቅናዎች እንዲያገኙ እና ስኬቶቻቸውን እንዲመዘግቡ ለመርዳት የእጅ መመሪያ መጽሃፍቶች አሉ።

በአንድ ቦታ ግዢ ማከናወን ይፈልጋሉ? ለ **Girl Scouts የሚያስፈልጉትን** ሁሉንም እቃዎች የያዘውን My Girl Scout Kit በአመቱ መጀመሪያ ላይ ይግዙ።

**የ Girl Scout ሱቅ** የሚፈልጓቸው ነገሮች በሙሉ ይዟል፡ በአካል ይሂዱ፣ ወይም በመስመር ላይ ወይም በስልክ ይዘዙ። ለበለጠ መረጃ Girl Scout shop ን www.gscnc.org/shop ላይ ይመልከቱ።

## የእውቅና አርማዎች እና ተለጣፊ ምልክቶች፡ ልዩነቱ ምንድን ነው?






### የእውቅና አርማዎች

በአንድ የተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የእውቀት ወይም የክህሎት መጨመርን የሚያመለክቱ እውቅና ያላቸው የ Girl Scout ሽልማቶች ናቸው። የሰደርያው ወይም መቀነት ፊት ላይ ይለበሳሉ

### ተለጣፊ ምልክቶች

በአንድ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍን የሚያመለክቱ ምልክቶች ናቸው። ተለጣፊ ምልክቶች በሰደርያው ወይም መቀነት ጀርባ ላይ ይለጠፋሉ

## የ Girl Scout ሱቆች፡

**ዋና ሱቅ (DC)** : 4301 Connecticut Ave NW, Washington DC 20008

**VA**: 5946 Centreville Crest Lane, Centreville, VA 20121

**MD**: 20201 Century Blvd፣ Germantown, MD 20874

**WV**: 153 McMillan Court, Martinsburg, WV 25404


የ Germantown፣ Centreville እና Martinsburg ሱቆች ወቅት ጠብቀው የሚሰሩ ናቸው-ከመሄድዎ በፊት የስራ ሰአቶችን gscnc.org ላይ ይመልከቱ!

# ዝግጁ፣ ቅንጁ፣ይመዝገቡ

ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? የመጀመሪያው እርምጃ የ Girl Scout አባል ሆኖ በይፋ መመዝገብ ነው። አንዴ ከተመዘገቡ በኋላ በአካባቢዎ ካሉ በጎ ፈቃደኞች ጋር ይገናኛሉ ከዛም አስደሳች ጉዞው ይጀምራል!

1. ወደ gscnc.org ይሂዱ እና 'ዛሬውኑ ይቀላቀሉ' የሚለውን ይጫኑ።
2. "ቡድኖች ፈልግ" የሚለውን ይጫኑ። ዚፕ ኮድ እና የ Girl Scout ልጅዎን የትምህርት ደረጃ ያስገቡ
3. ይበልጥ ተስማሚ የሆነውን ቡድን ይፈልጉ እና ወጣት አባላትን እና አዋቂ በጎ ፈቃደኞችን ለመጨመር የመደመር ምልክቱን ይጫኑ።
4. የአዋቂ ወላጅ/አሳዳጊ መረጃ ያስገቡ
5. የ Girl Scout ልጅዎን መረጃ ያስገቡ።
6. የሚቀላቀሉ ተጨማሪ የቤተሰብ አባላትን ያክሉ!
7. ቀጥሎም ክፍያ ያድርጉ ወይም የገንዘብ እገዛ ይጠይቁ - የማረጋገጫ ኢሜይል ይደርስዎታል፣ አሁን ዝግጁ ነዎት!

*እባክዎን የአባልነት ምዝገባ ክፍያ ተመላሽ የማይደረግ መሆኑን ልብ ይበሉ።*




**ማስታወሻዎች**

# ስለ እኔ ቡድን

የእርስዎን Girl Scout አስፈላጊ የቡድን መረጃ ለማጣቀሻነት እዚህ ያስቀምጡ!

**የቡድን ዋና-ዋና መረጃዎች**

የቡድን ቁጥር:-

ደረጃ:-

የስብሰባ ቀን እና ሰዓት:-

የአገልግሎት ክፍል:-

የስብሰባ ቦታ:-

ልጅዎን ለመውሰድ ከዘገዩ የሚኖር ሂደት፡

**የቡድን መሪ የመገኛ መረጃ**

ስም፡

ስልክ፡

ኢሜይል:-

ስም፡

ስልክ፡

ኢሜይል:-

ስም፡

ስልክ፡

ኢሜይል:-

**የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪ(ዎች) የመገኛ መረጃ**

ስም(ዎች):

ስልክ፡

ኢሜይል:-

**ሌሎች ዝርዝሮች/ማስታወሻዎች**

የቤተሰባችን የበጎ ፈቃድ ሚና:-

የ MyGS የተጠቃሚ ስም (ዋና ኢሜይል):-

የይለፍ ቃል:



## የ Girl Scout ቃል ኪዳን

የሚከተሉትን ለማድረግ እንደምሞክር፣ ቃሌን
እሰጣለሁ፡
ፈጣሪን እና ሀገሬን ለማገልገል፣
ሰዎችን ሁል ጊዜ ለመርዳት፣
እንዲሁም በ Girl Scout ህግ ለመተዳደር።

**የ Girl Scout ን ቃል-ኪዳን ሲገቡ፣ እያንዳንዱ አባላት "ፈጣሪ" የሚለውን ቃል ከራሳቸው መንፈሳዊ እምነት ጋር በሚስማማ ቃል መተካት ይችላሉ።*

## Girl Scout ህግ

የሚከተሉትን ለመሆን የተቻለኝን አደርጋለሁ
ሐቀኛ እና ፍትሃዊ፣
ተግባቢ እና ተባባሪ፣
በጎ እና አሳቢ፣
ደፋር እና ጠንካራ፣ እንዲሁም
ለምናገረው እና ለማደርገው ኃላፊነት የሚሰማኝ
እራሴን እና ሌሎችን ለማክበር፣
የበላይ አስተዳደርን ለማክበር፣
ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠቀም፣
ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠቀም፣
ዓለምን የተሻለ ቦታ ለማደረግ እንዲሁም።

girl scouts nation's capital